# እውነት ለመናገር የማይደፍር እንዴት ሽማግሌ ይሆናል?

የቀድሞ ቅንጅት አመራሮች ከእስር የተፈታንበትና አሁን እንደ አዲስ አነጋጋሪም አሳሳሪም የሆነው ጉዳይ 18 ወራት በፈጀ የሽምግልና ሂደት በሀገር ባህል የእርቅ መንፈስ የተፈፀመ ስለመሆኑ ሐምሌ 13 ቀን 1999 ዓ.ም. በዕለተ አርብ ታሣሪዎቹ ከቃሊቲ ግቢ ከመለቀቃችን አስቀድሞ የሂደቱ ተካፋይ የነበሩም ያልነበሩም ሽማግሌዎች ተሰባስበው በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሲናገሩ ተሰምተዋል፡፡ ፅፈው ባሠራጩት መግለጫም ይህንኑ ገልፀዋል፡፡ ከዛም ወዲህ በተለያየ ጊዜና መንገድ በተለያዩ ሰዎች ይሄው ተነግሮአል፡፡ ይህንኑ የሚያስረዳ በፅሑፍ የሠፈረ በድምፅ የተቀረፀ ብዙ ማስረጃም አለ፡፡

ታሣሪዎቹ ከእስር በተፈታን በ3ተኛው ቀን ማለትም ሰኞ ሐምሌ 16 ቀን 1999 ዓ.ም. ባወጣነው መግለጫ «በሀገራችን ይቅር መባባል መንፈስ፣ በሽምግልና ችግሩን ለመፍታት ተስማምተናል፡፡» በማለት መግለፃችንና አጠቃላይ ሂደቱን ግን ሽማግሌዎች ጊዜና ወቅት ሲያመቻቸው ሊገልፁት እንደሚችሉ እምነታችንን ገልፀን እንደነበረ ይታወሳል፡፡

ታዲያ ዛሬ ምን ተገኝቶ ምንስ አዲስ ነገር ተፈጥሮ ነው «በሽምግልና ነው የተፈታነው» ማለት ለማሳሰር ያበቃው፡፡ ነገሩ ከዚህ ደርሶ አንድዬዋን ሴት ፖለቲከኛ ለእስር ካበቃ ሽማግሌዎች ይናገሩታል ተብሎ የታለፈው እውነት ለአደባባይ መብቃት አለበት፡፡ «እርጥቡ ሬሳ ደረቅ አስነሳ» እንዲሉ ለጊዜ ትተን፣ ለሽማግሌዎች ሰጥተን የተውነውን ጉዳይ መንግሥት በእሱ ብሶ ከነካካው ወደ ኋላ ሄደን የነበረውን ሂደት መግለፅ ግድ ይሆናል፡፡

አጠቃላይ ሂደቱ 18 ወራት የፈጀ፣ ነገሩ እልባት ካገኘም ዓመት ከመንፈቅ ያስቆጠረ በመሆኑ ሁሉንም በዝርዝር ማስታወስ ይገዳልና የተሟላ መረጃ ለታሪክና ለትውልድ ለማቆየት በሂደቱ ውስጥ ያለፉ ሰዎችን ትውስታ ማጣመር ያስፈልጋል፡፡ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተን ሰዎችም በነገሩ ላይ ሊኖረን የሚችለው ማወቅ በሦስት ደረጃ ሊከፈል ይችላል፡፡

የመጀመሪያዎቹ የሽምግልናው ሂደት ቀጥተኛ ተካፋዮች፤ ሁለተኛዎቹ በመጀመሪያው ላይ የተገለፁት ሰዎች በታሠሩባቸው ዞኖች የሚገኙና መረጃውን በወቅቱ ከተደራዳሪዎቹ ያገኙ የነበሩት ሲሆኑ (የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ በዚህኛው ይመደባል) በሦስተኝነት የሚመደቡት ሂደቱን በሰሚ ሰሚ ይከታተሉት የነበሩ ናቸው፡፡ እነዚህ እንደ የምድባቸው ስለ ጉዳዮ ያላቸው ማወቅ የተለያየ የመሆኑን ያህል እንደ ሰዎቹ የማስታወስ ችሎታና በወቅቱ ለነገሮች ትኩረት ሰጥተው እንደ መከታተላቸው ይለያያል፡፡

ለዚህም ነው ሰለ 18 ወራቱ የሽምግልና ሂደት በቂ ስዕል መፍጠር የሚቻለው የተለያዩ ሰዎችን ትውስታ በማሰባሰብ ነው ለማለት የቻልኩት፡፡ ስለሆነም ለዚህ ግብዐት ይረዳ ዘንድ አዕምሮዬ የሚያስታውሰውን በዚህ ፅሑፍ ለመግለፅ እሞክራለሁ፡፡

## በማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ

እስራቱ የተጀመረው ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም. ሆኖ በዚህ ወር መጨረሻ ወይንም በኅዳር የመጀመሪያው ሳምንት ፕ/ር ኤፍሬም ይስሀቅና ፓስተር ዳንኤል እንዲሁም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት መጥተው ጉበኙን፡፡ ለማንበቢያ የሚሆን በቂ መብራት ያልነበራቸው የዕስር ክፍሎች በዚሁ ዕለት መብራቶቻቸው እንዲስተካከሉ ተደረገ፡፡ ከዛ በኋላ ሁሉንም ሳናያቸው ወደ ቃሊቲ ተላክን፡፡

## ፓስተር ዳንኤል መፃህፍት ይዘውልን መጡ

ቃሊቲ ከወረድን በኋላ ፓስተር ዳንኤል በድርጅታቸው ስም መፃህፍት አመጡልንና በዚሁ ግንኙነት ተጀመረ:: ጥቂት ቆይቶም ፐ/ር ኤፍሬምን በመያዝ ሽምግልና ሊጀምሩ እንደሚፈልጉ በመግለፅ ተወካዮቹን አመራሮች አነጋገሩ:: ሂደቱ የፈጀው 18 ወራት ነው ከሚለው ተነስተን በዕስር ከቆየንበት 21 ወራት ላይ ስንቀንሰው ሽምግልናው የተጀመረው በታሰርን በሦስተኛ ወር ነው ማለት ነው::

ይህ የሽምግልና ጅምር እያደገ ሄዶ በየጊዜው እነ ፐ/ር ኤፍሬም ይፈልጉዋችኋል እየተባሉ ከየዞኑ ተወካዮች እየተጠሩ ጠ/ሚኒስትሩ የሚሉትና የሚፈልጉት እየተነገራቸው እነርሱም ምላሻቸውን እየሰጡ አንዳንዴ ለወራት ሂደቱ እየተቋረጠ ፐ/ር ኤፍሬምና ፓስተር ዳንኤል ዋንኛ ተዋናይ ሆነው ሌሎች ከሦስትና አራት የማይበልጡ ሰዎች እየተቀያየሩ ሂደቱ ቀጠለ::

## የጠቅላይ ሚኒስትሩን ፍላጐት የያዘ የተባለ ደብዳቤ መጣ

ከቤተ መንግሥት ቃሊቲ በመመላለስ ብዙ የማግባባት ሂደት ከታለፈ በኋላ ጠ/ሚኒስትሩ የሚፈልጉትን ሀሣብ የያዘና (ራሳቸው የፃፉት ነው ተብሎም ነበር) እኛ እንድንፈርምበት የሚፈለግ ደብዳቤ ይዘው ሽማግሌዎቹ ቃሊቲ መጡ:: ታሳሪዎቹም በየዞናችን በተወካዮቻችን አማካኝነት መጥቶልን ከተወያየንበት በኋላ በዛ ደብዳቤ ላይ ልንፈርም እንደማንችል ገልፀን ማስተካከያ ያልነውን ሀሣብ አስፍረን መለስን:: ይህ ደብዳቤ ለብዙ ጊዜ ከቤተ-መንግሥት ቃሊቲ እየተመላለሰ ማስተካከያ ሲደረግበት ከቆየ በኋላ አንድ ወቅት ላይ «ጠ/ሚኒስትሩ ከዚህ ምንም የሚለወጥ ነገር አይኖርም ብለዋል» ተባለ:: በዚህም ሽማግሌዎቹ የማግባባት ጫናቸውን በእኛ ተወካዮች ላይ ማድረጉን መረጡ::

ሂደቱ በዚህ መልክ ቀጥሎ መግባባት ላይ መድረስ አስቸጋሪ ሆኖ ባለበት ሰዓት ሽማግሌዎቹ የተሻሻለ ያሉትን ደብዳቤ ይዘው መጡ:: ይህ የሆነው ግንቦት ውስጥ ይመስለኛል:: ይሄኛውም ቢሆን በእኛ ተወካዮች በኩል ሙሉ ለሙሉ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ማስተካከያ ተደርጐበት ተመለሰ:: ይህ በሆነ ማግስት የሰጣችሁትን ማስተካከያ ጠ/ሚኒስትሩ ተቀብለውት ደብዳቤው በአላችሁት መሠረት ተስተካክሏል በማለት ሽማግሌዎቹ ተመልሰው መጥተው በተናጠል ማስፈረም ጀመሩ:: በመካከሉ የደብዳቤውን ቅድመ ይዘት ያወቁት ከነበሩት ሰዎች መካከል ደብዳቤው በተባለው መልኩ ያለመስተካከሉን አረጋገጡ:: በዚህም የተጀመረው ፊርማ ተቋረጠ:: በቦታው የነበሩ የቅንጅት ኃላፊዎችም ፐ/ር ኤፍሬምን ለጥረታቸው አመስግነው ሁለተኛ አትምጣብን ብለው ሸኙአቸው::

## የሕግ ባለሙያው አቶ ታምሩ ወ/አገኝ ሽምግልናውን መቀላቀል

ከላይ የተገለፀው ድርጊት ከተፈፀመ ቀናት ከአለፈ በኋላ ፐ/ር ኤፍሬም አቶ ታምሩን ይዘው በመምጣት ከየዞኑ ተደራዳሪዎችን አስጠርተው የተቋረጠውን ሂደት ማስቀጠል በሚቻልበት ሁኔታ ላይ የሚያስኬድ ቀዳዳ ካለ በሚል ነው አቶ ታምሩን ይዤ የመጣሁት በማለት ተወያዩ:: በዚህ እንደገና ጅማሮ ሂደቱ ቀጥሎ ወደ ስምምነት ሲቃረብ የቅንጅት ላዕላይ ም/ቤት አባላት በሙሉ በአንድ ላይ ተሰብስበው መወሰን አለባቸው የሚል ጥያቄ በእኛ ተወካዮች ቀረበ:: ፐ/ር ኤፍሬምም ይህንኑ ለጠ/ሚኒስትሩ ነግረው በእሳቸው ፈቃድ በቃሊቲ ወህኒ ቤት ስብሰባ ለማካሄድ በቃን::

## የቅንጅት ም/ቤት አባላት ስብሰባ በቃሊቲ ወህኒ ቤት

በተመደበልን አነስተኛ አዳራሽ ተገናኝተን ልንነጋገር ስንል ፖሊስ መካከላችሁ መገኘት አለበት በመባሉ ያለመስማማት ተፈጥሮ በግልፅ ልታዩን በምትችሉበት ሁኔታ በሜዳ ላይ እንሰበሰባለን ብለን በዚሁ መልክ የመጀመሪያውን ስብሰባ አደረግን። ሁለተኛውን ስብሰባችንን ፖሊስ መካከላችን ሳይኖር ለመሰብሰብ ተስማምተው በአዳራሽ ውስጥ አደረግን። ነገር ግን ይህን ስብሰባችንን በምስጢር ቀድተው እያንዳንዱ ሰው የተናገረውን በአይጋ ፎረም ዌብ ሳይት ላይ አወጡት። አስገራሚው ነገር ይህንኑ በአይጋ ፎረም ላይ የወጣ ፅሑፍ አባዝተው እኛ ለዘመድ ጥየቃ ስንወጣ በየዞናችን አንድ አንድ ሰው ፍራሽ ሥር አስቀምጠውት አገኘን።

በአጠቃላይ በቃሊቲ ያደረግነው ሦስት ወይንም አራት ስብሰባ ይሆናል። በዚህ ወቅት በህግ ባለሙያው አቶ ታምሩ ወ/አገኝ የተነገረን «እነዚህ ሰዎች ሁለተኛ አጠገባችን እንዳትመጣ ብለው አባረሩኝ እባክህ ይህን ሂደት መቀጠል የሚቻልበት የህግ ቀዳዳ ካለ ብትረዳኝ ብለውኝ ነው እኔ የመጣሁት። ይህ እነ ፕ/ር ኤፍሬም ይስሀቅ የያዙት ጉዳይ የሚስተናገደው ከሦስት መንገድ በአንዱ ነው። ይቅርታ፣ ምህረት፣ ክስ ማቋረጥ። ሁለቱ የመጀመሪያዎቹ ተግባራዊ የሚሆኑት ከፍርድ በኋላ ነው። የእናንተ ጉዳይ ፍርድ ያልተሰጠበት በመሆኑ ሊስተናገድ የሚችለው በይቅርታ ማቋረጥ ነው።» የሚል የህግ ማብራሪያ ነበር።

ፕ/ር ኤፍሬምም እነርሱ ይፈርሙ እንጂ እኔ ክሱ እንዲቋረጥ አደርጋለሁ በማለት ጠ/ሚኒስትሩ አረጋግጠውልኛል አሉ። ይህን መነሻ በማድረግ እነርሱን አስወጥተን ብዙ ተወያየን።

## ሰኔ 15 ቀን 1998 ዓ.ም. ፊርማችንን ያኖርንበት ዕለት

ከየዞናችን ተጠርተን ወደ ስብሰባ አዳራሽ የምንወስደው ፕ/ር ኤፍሬም ቃሊቲ ደርሰው በጠ/ሚኒስትሩ መፈቀዱ ሲረጋገጥ ነው። በዚህ ዕለትም ለመጨረሻ ጊዜ በአዳራሹ ተገናኘን። ከፕ/ር ኤፍሬም ጋር የመጡት አቶ ታምሩ ጉዳዮ ስለሚገኝበት ደረጃ ተጨማሪ ማብራሪያ ከሰጡን በኋላ ፕ/ር ኤፍሬም «ሲወጡ ይደርሱበት የለም ወይ ምነው እዛ ስብሰባ አበዙ ብለዋችኋል ጠ/ሚኒስትሩ» አሉን። ቀጥለውም እኔ ነገ ወደ አሜሪካ ልሄድ ተነስቼ ነበር ነገር ግን ጠርተውኝ ለምን ይህንን ጉዳይ አንድ መልክ አስይዘህልኝ አትሄድም ብታስፈርምልኝ እኮ እኔ ቅዳሜ ለሥራ ባልደረቦቼ አቅርቤ ሰኞና ማክሰኞ የመፈቻ ወረቀት ሰጥቼህ አስፈትተሀቸው ትሄዳለህ ብለውኝ ነው የቀረሁት። እሳቸው ይህ ጉዳይ በቶሎ እንዲያልቅ በጣም ይፈልጋሉ እባካችሁ ወንድሞቼ አባቶች ብለው ተንበርክከው እያለቀሱ ለመኑን። ቀጥለውም በጣም የምወደው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ብለው (ትንቢተ ኤርምያስ ወይንም ትንቢተ ኢሳያስ አሁን መለየት አልቻልኩም) የተወሰነ ጥቅስ በቃላቸው ነገሩን።

ከዚህ በኋላ እነርሱ ወጥተው እኛ የመጨረሻችን የሆነውን ውይይት አካሄደን መስማማት ላይ ስንደርስ ጠርተናቸው ከእነርሱ ጋር መስማማት ባስፈለገን ጉዳይ ላይ ተወያይተን፡-

1. እኛ የምንፈርምበት ደብዳቤ ለሽማግሌዎች ሆኖ እነርሱ የእኛን ፊርማ ከያዙ በኋላ ለጠ/ሚኒስትሩ ደብዳቤ እንዲፅፉ፣
2. ክሱ እንደሚቋረጥና ለፍርድ የተቀጠረው ችሎት እንደማይካሄድ፣
3. ስምምነቱን የትኛውም ወገን ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ እንዳያውለው፣

4. ጉዳዩ ለሕዝብ የሚገለፀው ሽማግሌዎች ባሉበት ሁለቱ ወገኖች መንግሥትና ከእስር ተፈቺዎች ግራ ቀኝ ሆነን እንደሚሆን፣
5. አጠቃላይ ሀገራዊውን ጉዳይ ከምርጫ 97 በፊት ወደ ነበረው ሁኔታ መመለስ የሚያስችል የፖለቲካ ውይይት እንደሚኖር ከስምምነት ላይ ደርሰን ለፐ/ር ኤፍሬምና ለሀገር ሽማግሌዎች የሚል አድራሻ በያዘና ከሥር የስምና የመፈረሚያ ቦታ ተዘጋጅቶለት ተባዝቶ በመጣ ወረቀት ላይ ፈረምን:: ለፐ/ር ኤፍሬምና ለሀገር ሽማግሌዎች የሚለው አድራሻ ለሀገር ሽማግሌዎች ብቻ ለምን እንዳልተባለ ራሴን መጠየቅ የጀመርኩት አሁን ነው::

## *ቃል የእምነት ዕዳ ሳይሆን ቀረ*

አርብ ከ12:00 ሰዓት በኋላ ፊርማችን ያረፈበትን ደብዳቤ ይዘው ከቃሊቲ የወጡት እነ ፐ/ር ኤፍሬም ሰኞ ሰኔ 18 ቀን 1998 ዓ.ም. የመጡት በተገባላቸው ቃል መሠረት የመፈቻ ወረቀት ይዘው ሳይሆን ጠ/ሚኒስትሩ ትንሽ ታገሱኝ ብለዋል የሚል የመማለጃ ቃል ይዘው ነበር::

ተወካዮቻችን ጠረተው የነገሩዋቸውና በእነርሱ አማካኝነት ለእኛም የተነገረን ጠ/ሚኒስትሩ «በተለይ በትግራይ ሕዝብ ስም የተደራጁ ቡድኖች በውጪ ኃይል ተፅዕኖ እጁን ተጠምዝዞ ነው የሚፈታቸው እያሉ ፕሮፓጋንዳ እየነዛቡኝ ስለሆነ ይህ ሁኔታ ረገብ እስከሚል አንድ አሥራ አምስት ቀን ታገሡኝ ብለዋል::» የሚል ነበር::

ይህ መልዕክት በደረሰን ሰሞን ጠ/ሚኒስትሩ ፓርላማ ቀርበው ባልተለመደ ሁኔታ የኢህአዲግ አባል የሆነ የፓርላማ አባል የእኛን ጉዳይ አንስቶ ጠየቀ:: እሳቸውም በፍ/ቤት ሂደት ጣልቃ አንገባም የሚባለው ይቅርታ ከፍርድ በኋላ የሚታይ ይሆናል የሚል ዓይነት መልስ ሲሰጡ ጠ/ሚኒስትሩ በሽማግሌዎቹ በኩል እንዲገለፅልን በችግር ውስጥ ሆነው ይሆናል ከማለት አልፈን በኋላ እንደሆነው ዓይነት ሽምጥጥ ያለ ክህደት ይፈፅማሉ ብለን ብዙዎቻችን አልገመትንም ነበር:: አንዳንዶቹ ግን ፊርማችንን እጃቸው ካስገቡ በኋላ የሚፈልጉትን ሊሠሩ ነው በማለት በቁጭት ይናገሩ ነበር::

## *የማስመሰያው ችሎት ቀጠለ*

የሽምግልናውን ሂደት መሞቅና መቀዝቀዝን ተከትሎ ሲካሄድ የቆየው የፖለቲካ ችሎት ይቋረጣል ተብሎ ቃል ተገብቶልን ከፈረምን በኋላ እንዲቀጥል ተደረገ:: በዕለቱ ወደ ችሎት ስንወሰድም ሆነ ዳኞቹ የዕድሜ ልክ እስራት ሲፈርዱብን ብዙዎቻችን ጉዳዩን እንደቀልድ ብሎም የድብብቆሽ ጨዋታ ያህል ነበር ያየነው:: ይህንን ያረጋገጠው ደግሞ የእድሜ ልክ እስራት ተፈረደባቸው ከሚለው ዜና ቀጥሎ የተነገረው የይቅርታ ጥያቄአቸው በጠ/ሚኒስትሩ አማካኝነት ለይቅርታ ቦርድ ተመራ የሚለው ዜና ነው:: ይህም እኛ ብቻ ሳንሆን ይህን ዜና የተከታተለ ሁሉ የድብብቆሽ ጨዋታውን በሚገባ እንዲረዳው ያስቻለን ነበር::

## *የሐምሌ 13 ቀን 1998 ዓ.ም. የቃሊቲ ማረሚያ ቤት ኃላፊዎች ጥድፊያ*

የእድሜ ልክ እስራት የተፈረደብን ሐምሌ 9 ቀን 1998 ዓ.ም. በተሰየመው «የፌዝ ችሎት» ስለነበረ ሐምሌ 13 ቀን 1998 ዓ.ም. እንፈታለን የሚል ግምት ስላልነበረን በየዞናችን ተረጋግተን የተለመደ የቀን ውሎአችንን በመጀመር ላይ እያለን በርካታ ነጫጭ ሚኒ ባሶች እየገቡ እንደሆነና ምን

እልባትም ከእኛ ጋር ለተያያዘ ጉዳይ ሊሆን እንደሚችል መረጃ ደረሰን:: ብዙም ሳይቆይ እየተጠራን እንሰበሰብበት ወደ ነበረው አዳራሽ ተወሰድን:: ወዲያው የቴሌቪዥንና የፎቶ ግራፍ ካሜራ የያዙ ሰዎች ወደ አዳራሹ ገቡ:: ለመቀረፅ ፍቃደኛ ያለመሆናችንን ገለፀን እንዲወጡ አስደረግን::

የማረሚያ ቤቶች ም/ል ኃላፊ መሆናቸውን የነገሩን ሰው ቀረፃው እንዲካሄድ ለማግባባት ቢሞክሩም ሂደቱ በየትኛውም ወገን ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ እንዳይውል ስለተስማማን አይቻልም ብለን በአቋማችን ፀናን::

ከዛም «እንኳን ደስ አላችሁ ከአሁኑ ሰዓት ጀምሮ ነፃ ናችሁ» በማለት በሀገሪቱ ፕሬዝዳንት የተፈረመውን የይቅርታ ምስክር ወረቀት ሰጡን:: ቀጥለውም ዕቃችሁን በሌላ ቀን መጥታችሁ ትወስዳላችሁ አሁን መኪና አዘጋጅተናል በየአቅራቢያችሁ ተመዳደቡና በየመኪናው ግቡ አሉን::

እኛ ደግሞ ቢያንስ አብረውን ሊወጡ የሚገቡ ዕቃዎቻችንን መያዝ አለብን ብለን ወደየ ዞናችን ሄድን:: የግቢው ኃላፊዎችም ተከትለው «እባካችሁ ቶሎ ውጡ ዕቃችሁን ነገ ከነገ ወዲያ ትወስዳላችሁ» እያሉ ሲያጣድፉን ከምኔው በተገላገልናቸው ያሉ ይመስል ነበር:: የያዝነውን ይዘን በየመኪናው ተሳፍረን በየቤታችን አደረሱን:: በዕለቱ ቀኑን ሙሉ የመንግሥት ዜና ማሠራጫዎች ዜናም ይሄው ነበር:: ከዚህ በፊት ግን ስምምነቱ ፈርሶ የተገባው ቃል ተጥሶ ከፈረምን በኋላ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ተሠርቶብናል:: አድማጭ አልነበረውም እንጂ::

በዚህ መልኩ ከእስር ከወጣን በኋላ ለአንድ ዓመት ከስድስት ወር በተለያየ አጋጣሚ የተገለፀው ይሄው ነው:: እንዲያውም ሽማግሌዎቹ ያላስጨረሱት ነገር አለ እየተባለም ይወቀሱ ነበር:: እስከ ቅርብ ጊዜ ከምርጫ 97 ጋር በተያያዘ ታስረው ያልተፈቱ ዜጎችን ለማስፈታት «ሽማግሌዎቹ» ይንቀሳቀሱ ነበር::

ታዲያ ዛሬ ይህን የሽማግሌዎችን ጥረትና ውጤት አፈርድሜ የሚያበላ ምክንያት ምን ተገኘ:: ከይቅርታ አዋጅ ቁጥር 395/96 ጋር የሚገናኝ አንድም ሂደት ያልተከናወነበትንና «በሀገር ባህል የይቅርታ መንፈስ የተከናወነ» ተብሎ የተመሠከረለትን ይቅርታ በህግና በህግ የተከናወነ ነው ብሎ ለመሞገት የሚያበቃ ምን የህግ ጭብጥ ተገኘ?

ማን ይናገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ የሚለውን ብሂል ለሽማግሌዎቹ መንገር ልጅ ለእናቷ ምጥ አስተማረች ይሆንብኛል:: ሽማግሌዎቹ ደግሞ ስለ ጉዳዩ ለመናገር ከዛሬ የባሰ ቀን ያለ አይመስለኝም:: እንዲያውም መናገር ብቻ ሳይሆን ያስታረቅነው በዚህ መንገድ ነው፣ ያስማማነው ይህን ይህን ብለን ነው ብለው ሊሞግቱ ይገባል:: ይህን ማድረግ ካልቻሉ በወ/ት ብርቱካን መታሠር ትውልዱ ጣቱን ወደ እነርሱ ይቀስራል:: የታሪክና የትውልድ ተጠየቂነትም ይኖራል:: እነርሱ እድሜያቸው ቢገፋም ልጅና የልጅ ልጅ ብሎም ዘመድ ወዳጅ በድርጊቱ ያፍራል::

እንደ ደጃዝማች ዶ/ር ዘውዴ ገ/ሥላሴ እውነቱን ሳትናገሩ ሞት ቢቀድማችሁ በዛኛውም ቤት አይመቻችሁም::